ጉድ በል ወገን፤ ቤተ ክርስቲያናችን የውሸት መድረክ ሆነች!!

ጥያቄ 1 ፥ ማንም ሰው ተነስቶ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ለንደን ቤተ ክርስቲያንን በካምፓኒም ሆነ በማንኛውም ስም ማስመዝገብ ይችላል ወይ?

ጥያቄ 2፥ ቤተ ክርስቲያናንን በስማቸው የያዙ ባለ አደራዎች ሣይፈቅዱ ወይንም ሳይፈርሱ አንድ ተራ ደረሰኝ እንኳን ማውጣት ይቻላል?

ጥያቄ 3፥ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው ሳያውቅ ወይንም ሣይፈቅድ አንድ ተራ ደብዳቤም እንኳን በቤተ ክርስቲያን ስም ሊወጣ ይችላል ወይ?

ጥያቄ 4፥ እንዴት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታዲያ በሁለት ተራ አባላት በካምፓኒ ትገዛለች? መልሱን እርሶ እራሶን ይጠይቁ

ጥያቄ5፥ በካምፓኒ ስም ተመዘገበች የተባለችው ደብረ ጽዮን ለንደን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አድራሻ ለምን የግለሰቦች አድራሻ ሆነ?

እነዚህንና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች በመጠየቅ የሚሰሙትን ወይም የሚነገሮትን ውሸት ይፈትሹ። ይህ ባይሆን ግን ቤተ ክርስቲያናችንን ሊያሳጣ የሚችል የተቀነባበረ ሴራ ሰለባ እንዳይሆኑ ይጠንቀቁ እያልን በዚህም አጋጋ ቤተ ክርስቲያችንን ለማዳን የሚከራከሩትን አቶ ግርማ ተሊላ እና አቶ ጥላዬ የሻነውን ለማስወገድ የተበየነውን ፍርደ ገምድል ብይን እውነታ ከዚህ በታች እንመልከት።

ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተች፤ 40 ዓመት ሊሞላት ነው። ከብዙ ዓመታት ጥረት በኋላም በልጆቿ ጥረት፤ ባተርሲ የሚገኘውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና፤ ቪከሬጅ. በ £1,700,000 ፓውንድ ገዝታለች። ለግዢውም፤ የገባችሁን ዕዳ ባጭር ጊዜ ውስጥ መክፈልም ችላለች። ከዚያም ባሻገር፤ የቤተ ክርስቲያኗ፤ አባላትና፤ ገቢም እየጨመረ መጥቷል። ይህንንም ለማድረግ ላስቻለን ቸሩ እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን።

ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲያናችን የውስጥ ደንብና በቻሪቲ ኮሚሽን የተመዘገበችበት ትረስት ዲድ፤ ከእድገቷ ጋር የማይመጣጠኑና፤ ብዙ አደገኛ ክፍተቶችና ጉድለቶች ያሏቸው ናቸው። ስለዚህም ሁለቱም ሰነዶች እንዲስተካከሉ የደንብ አሻሻይ ኮሚቴ ከመቋቋሙም በላይ፤ የሰበካ አስተዳደሩም ዕድሜ ደንቡ ተስተካክሎ እስከሚጸድቅ ድረስ ከተራዘመ ሶስት ዓመት ሊሞላው ነው።

በደንቡ ድክመት ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችን በእንግሊዝ አገር ሕግ መሰረት ሕጋዊ ሰውነት የላትም። በመሆኑም የቤተ ክርስቲያኗ ሕንፃ በአራት ግለሰቦች (አባ ግርማ፣ ቄስ ዳዊት፣ ወዘሪት ትግዕስትና አቶ ታዬ) በባለ ሙሉ ባለቤትነት ተይዞ ይገኛል። ይህም በጣም አደገኛ መሆኑን ሁላችንም የምንረዳው ነው። በመሆኑም በውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ላይ ቤተ ክርስቲያናችን Charitable Company limited by Guarantee ብታቋቁምና በካምፓኒ ሀውስ ብታስመዘግበው ንብረቷን በራሷ ስም መያዝ ትችላለች በራሷ ስም መዋዋል ትችላለች።

በውይይቱ ሰዓት አንዳንድ ካህናት፤ በተለይም መሪጌታ አለማየሁ ካምፓኒ ሀውስ ስሙን ሊከለክለን ይችላል፤ ስሙን ሌላ ሀይል ቢይዝብንስ? ብለው ተናገሩ። ይህም አነጋገር በጣም አሳሰበን፤ ስለዚህም አቶ ግርማ ተሊላና አቶ ጥላዬ የሻነው ከብዙ አባላት ጋር በግልፅ ተነጋግረው፤ REESE DBARAT LONDON DEBRE TSION ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH የሚባል አዲስ ድርጅት በካምፓኒ ሀውስ አስመዘገቡ። ይህ ባተርሲ ከምትገኘው ቤተ ክርስቲያናችን ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ሲሆን፤ ይህ የተደረገበተም ምክንያት የቤተ

ክርስቲያናችንን ስም በተንኮለኞች ከመወሰድ ለማዳን ሲባል ነው። የተመዘገበውም ድርጅት ከስም የመያዝ ምዝገባ በስተቀር ምንም አይነት እንቅስቃሴ አላደረገም።

ሰሞኑን ደግሞ ሌሎች ግለሰቦች እንደፈራነው ስሙን ለማስመዝገብ ሲያጣሩ እንደማይችሉና ስሙም በሌሎች እንደተያዘ ተነገራቸው። ለመሆኑ ስሙን ለምን ፈለጉት? ይህን ድርጊት እንደሰሙ፤ አቶ ግርማና አቶ ጥላዬ፤ ይህን የተመዘገበ ስም፤ ቤተ ክርስቲያናችን ስትፈልገው በነፃ እንደሚሰጡና፤ ካልፈለገችውም ስሙን እንደሚያሰርዙትና ስሙን የያዙበትንም ምክንያት ገልፀው ደብዳቤ ለሰበካ አስተዳደሩ አስገቡ። እሁድ (23/12/12) ከጠዋቱ አራት ስአት ላይ ከ20 በላይ የሚሆኑ የቤተ ክርስቲያኗ አባላት ወደ ጽሕፈት ቤት በመሄድ፤ ለዋና ፀሐፊው ስለጉዳዩ አስረድተው ይህ ነገር ለሕዝብ ከተነገረ ሙሉ ለሙሉ እንዲነገርና፤ ለአቶ ግርማና ለአቶ ጥላዬም የመናገር መብት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ፀሐፊው (ዳዊት ገ/ዮሐንስ) 'የወሰነውን እንናገራለን፤ እርሱንም አዚያው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሄዳችሁ ስሙ፤ አሁን አልነግራችሁም' በማለት በእልህና በንቀት መለሳቸው።

ከዚያም በዓውደ ምሕረት ላይ አቶ ግርማና አቶ ጥላዬ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ካምፓኒ አድርገው አስመዝግበዋል። ራሳቸውን የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪና ፀሐፊ አድርገው ሾመዋል ብለው ዋሹ። የአቶ ግርማንና የአቶ ጥላዬንም የቤት የግል አድራሻ፤ በስክሪን ላያ አሳዩ በመደጋገምም አነበቡትም። በእነዚህ ግለሰቦች ላይ አንድ አደጋ ቢደርስ፤ በሕግ ተጠያቂ የሚሆኑት፤ የሰባካ አስተዳደር ጉባኤው አባላት ናቸው። ይህም ለፖሊስ ሪፖርት ተደርጓል። እነዚህ ሁለት አባላት፤ ለቤተ ክርስቲኗ በማሰብ በራሳቸው ወጪ ላደረጉት ተግባር ምስጋና ሲገባቸው፤ ተኮነኑ፣ ተወገዙ፣ ለአደጋም ተጋለጡ። እጅግ በጣም የሚያሳዝነው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው አባላትና ካህናት፤ የተነገረው ነገር በጣም አደገኛ ውሸት መሆኑን እያወቁ፤ እንደተለመደው በዓውደ ምሕረት ላይ ቆመው ዋሹ ሕዝብን አሳሳቱ። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን፤ እንደተለመደው የጥምር ጉባኤን ሳያማክሩ ከአባልነት አገዱ። አድራሻቸውን በግልፅ አውጥተው ለአደጋ አጋለጧቸው። ከእዚህ በፊት መሪጌታ አለማየሁና አባ ግርማ "ለሃይሞኖቱ የሚሞት ምነው ጠፋ" በማለት በዓውደ ምሕረት ላይ ጥሪ ሲያደርጉ ነበር።

የእዚህ ሁሉ አደገኛ ውሸት አስተባባሪና መሪ አባ ግርማ ከበደና መሪጌታ አለማየሁ ናቸው (እነዚ ሁለት ግለሰቦች ከአንድ ሺ እና ከአንድ ሺ ፓውንድ በላይ በወር ደሞዝ ተከፋይ ሲሆኑ፤ አባ ግርማ ከዚህ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን እንደ ባንክ ተቆጥራ፤ ሕገ ቤተ ክርስቲያንም እንደሚለው ጠቅላላ ጉባኤው ሳያውቀው ብድር እየተባለ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚወስዱ በቻሪቲ ኮምሽን ዘገባላይ አይተናል፤ መሪጌታ አለማየሁም ከዚህ በፊት ቤተ ክርስቲያናችችንን ማዘጋታቸው አልበቃቸው ብሎ፤ በቅርቡ ደግሞ CRB ቼክ አላደርግም በማለት ቤተ ክርስቲያናችንን ከፍተኛ አደጋላይ የጣሉ ግለሰብ ናቸው)። ሌሎችም የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላትና ካህናትም ተጠያቂ ናቸው። የእዚህ ሁሉ ዋና ምክንያት፤ የገንዘብና የስልጣን ሽሚያ ሲሆን፤ የሃይማኖት መሪነታቸውን ረስተው፣ ሃይማኖትን ለዚህ መሰሪ ተግባራቸው ሽፋን አድርገው በመጠቀም ላይ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኗንም በአዲስ አበባ ቁጥጥርና ባለቤትነት ስር ለማድረግ ብዙ አዲስ ሰዎችን እያሰባሰቡ ነው።

የእነዚህም የአዲስ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፤ ስለዚህ አባላት ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ መጥታችሁ መብታችሁን ካላስከበራችሁ እነዚህ ውሸታሞች ለጥቅምና ለሹመት ብለው ቤተ ክርስቲያኗን አሳልፈው ለመስጠት ትንሽ ነው የቀራቸው። ከተባበርን እናሰቆማቸዋለን። ስለዚህ ኑ መብታችሁን አስከብሩ ቤተ ክርስቲያናችሁን አድኑ። በ30/12/12 እሑድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተገኙ። በእዚህ ሳምንት ውስጥም፤ ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር ስብሰባ እንጠራለንና ተከታተሉ በስብሰባውም ላይ ተገኝታችሁ ስለሁኔታው ተረዱ። እናንተም በምትችሉት ሁሉ ተራድታችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁን አድኑ።

እግዚአብሔር ይታደገን!

ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ

ለንደን

19th December 2012

<u>ስለ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያነ ምዝገባ</u>

ቤተ ክርስቲያናችን፤ በካምፓኒ ሃውስ Charitable Company Limited by Guarantee ለማቋቋም፤ አባላት ላለፉት ብዙ ወራት በውይይት ላይ መሆናችን የሚታወስ ነው። የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ግን ገና አልተደረሰም።

ስለዚህም፤ ለቤተ ክርስቲያኗ፤ ተገቢ የሆነውን ሰው፤ ሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንዳይውስድባት በማሰብ፡ እኛ አቶ ግርማ ተሊላና፤ አቶ ጥላየ የሻነው በሰማችን REESE ADBARAT SAINT MARY OF LONDON DEBRE TSION ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH የተባለ Company Limited by Guarantee በCompanies House ማስመዝገባችንን እያሳወቅን፤ የቤተ ክርስቲያኗ አባላት፤ ካምፓኒ ሊሚትድ ባይ ጋራንቲ፤ ለማቋቋም ሲወስኑ፤ ያስመዘገብነውን ድርጅት በነፃ ለቤተ ክርስቲያኗ እንደምናስተላልፍና፤ ወይም አባላት charitable company limited by guarantee ላለማቋቋም ከወሰኑ ደግሞ ያስመዘገብነውን ድርጅት፤ ወዲያውኑ እንደምንዘጋ፤ ለሰበካ አስተዳደሩ ለማስታወቅ እንወዳለን።

እግዚአብሔር ይመስገን

ግርማ ተሊላ　　　　　　　　　　ጥላየ የሻነው

ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
Re'ese Adbarat St. Mary of Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, London

ታህሣሥ ፲፫ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.
Date: 22 December 2012
Ref: DTM-568-Ext-MSL-00568/12

ለአቶ ግርማ ተሊላ
ለአቶ ጥላየ የሻነው

ጉዳዩ፡- <u>ከቤተክርስቲያን አባልነት መታገድዎን ይመለከታል፤</u>

ከካምፓኒ ሃውስ (Company House) በተገኘ መረጃ መሠረት እርስዎ በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስም በግል ሥልጣንዎ Reese Adbarat Saint Mary of London Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church LTD (Company No 8200045) "ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ" (Company Limited by Guarantee) አቋቁመው በስውር በ 4 September 2012 በግል የመኖሪያ ቤት አድራሻዎ ማስመዝገብዎንና ይህንኑም ከሦስት ወራት በላይ ደብቀው መቆየትዎ ተደርሶበታል።

ይህን አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው ለፖሊስና ለሕግ አካላት አሳውቋል። ጉዳዩ ሕጋዊ መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ እርስዎ ከቤተክርስቲያን አባልነትዎ ለጊዜው እንዲታገዱ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ተወስኗል።

ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጠር ማንኛውም ውዝግብና ጠብ እርስዎ በሕግ የሚጠየቁ መሆኑን በጥብቅ እናሳስባለን።

ሰላመ እግዚአብሔር አይለየን !

የደብሩ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ

ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

Re'ese Adbarat St. Mary of Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, London

ታህሣሥ ፲፫ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.
Date: 22 December 2012
Ref: DTM-568-Ext-MSL-00568/12

ለአቶ ግርማ ተሊላ
ለአቶ ጥላየ የሻነው

ጉዳዩ፡- <u>ከቤተክርስቲያን አባልነት መታገድዎን ይመለከታል፤</u>

ከካምፓኒ ሃውስ (Company House) በተገኘ መረጃ መሠረት እርስዎ በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስም በግል ሥልጣንዎ Reese Adbarat Saint Mary of London Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church LTD (Company No 8200045) "ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ" (Company Limited by Guarantee) አቋቁመው በስውር በ 4 September 2012 በግል የመኖሪያ ቤት አድራሻዎ ማስመዝገብዎንና ይህንኑም ከሦስት ወራት በላይ ደብቀው መቆየትዎ ተደርሶበታል።

ይህን አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው ለፖሊስና ለሕግ አካላት አሳውቋል። ጉዳዩ ሕጋዊ መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ እርስዎ ከቤተክርስቲያን አባልነትዎ ለጊዜው እንዲታገዱ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ተወስኗል።

ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጠር ማንኛውም ውዝግብና ጠብ እርስዎ በሕግ የሚጠየቁ መሆኑን በጥብቅ እናሳስባለን።

ሰላመ እግዚአብሐር አይለየን !

የደብሩ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ

St Mary of Debre Tsion, Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, 1 St. Philip Square, Queenstown Road, Battersea, London, SW8 3RT
Registered Charity No: 1060394